# ማጠቃለያ

# ግረንፈል ታወር ጥያቄ የመንግስት የሂደት ሪፖርት

ታህሳስ 2025

## ይዘቶች


አጠቃላይ እይታ 2

መግቢያ 2

የማስፈጸሚያ የጊዜ ሰሌዳ 2

የየካቲት ዓመታዊ ሪፖርት 3

ሰፋ ያለ ማሻሻያዎችን በተመለከተ አዲስ መረጃ 3

- የአደጋ ስጋቶችን ማስወገድ ስራን የማፋጠን እቅድ (RAP) 3
- የከፍተኛ ስጋት ህንጻዎች ቁጥጥር አሰራር 4
- ማህበራዊ መኖሪያ ቤት ማሻሻያዎች 5
- ግልጽነት እና ቁጥጥር 5

ምክረ-ሃሳቦች ላይ ማጠቃለያ ዝማኔ 6

የግንባታ ኢንዱስትሪ 6

ነጠላ የግንባታ ተቆጣጣሪ 6

ከፍተኛ ስጋት ያለባቸው ህንጻዎች ትርጉም 6

- የመንግስት አሰራሮች 7
- የእሳት አደጋ መሐንዲሶች 7
- የግንባታ ቁጥጥር 8

የእሳት እና ነብስ አድን አገልግሎቶች 8

- የእሳት እና ነብስ አድን ኰሌጅ 8
- የብሄራዊ እሳት አደጋ ዋና አለቆች ምክርቤት(NFCC) እና የለንደን እሳት አደጋ ብርጌድ (LFB) 8

ምላሽ እና ማገገም 8

ለአደጋ ተጋላጭ ሰዎች 9

- የመኖሪያ ቤቶች ግላዊ የአደጋ ጊዜ ሽሽት ዕቅዶች (RPEEPs) 9

## አጠቃላይ እይታ

| የውይይት ርዕሰ ጉዳይ | የምከረ ሃሳቦች ቁጥር | በሂደት ላይ ያለ | የተፈጸመ |
|---|---|---|---|
| የግንባታ ኢንዱስትሪ | 28 | 25 | 3 |
| የእሳት እና የነብስ አድን አገልግሎቶች | 13 | 12 | 1 |
| ምላሽ እና ማገገም | 14 | 14 | 0 |
| ለአደጋ ተጋላጭ ሰዎች እና ደረጃ 1 ምክረ-ሃሳቦች | 6 | 2 | 4 |
| **ድምር** | **61** | **53** | **8** |

## መግቢያ

ይህ በግሬንፈል ታወር ማጣሪያ ፡ ደረጃ 2 ምክረሃሳቦች ላይ የመንግስት ሶስተኛው የሂደት ሪፖርት ነው። ይህ የሂደት ሪፖርት እትም፡ ከንጥል የግንባታ ተቆጣጣሪ ዝርዝር መረጃ እና ምክክር፣ የእሳት ምህንድስና ባለስልጣን መግለጫ እና የቀጣይ ደረጃ ሰነድ እንዲሁም የግንባታ ደህንነት ተቆጣጣሪ የከፍተኛ ስጋት ግንባታዎች ትርጉሞች ግምገማ ግኝቶች ጎን ለጎን የታተመ ነው።

መንግስት ሁሉንም የማጣሪያውን ግኝቶች ተቀብሏል እንዲሁም የበለጠ ጠንካራ አ ታማኝ የቁጥጥር አሰራር ለመገንባት እና አሰተማማኝ፣ ጥራት የጠበቁ መኖሪያ ቤቶችን ለሁሉም ለማቅረብ በሁሉም 58 ምክረሃሳቦች ላይ እርምጃ በመውሰድ ላይ ይገኛል።

ከመስከረሙ የሂደት ሪፖርት በኋላ ሌሎች አምስት ተጨማሪ ምክረሃሳቦችን ተግብረን ጨርሰናል። ከግንባታ ኢንዱስትሪ ጋር የተያያዙ ምክረሃሳቦች 2፣ 17 እና 25 ከእሳት እና የነብስ አድን አገልግሎቶትች ጋር የተያያዘ ምክረ ሃሳብ 39 ለአደጋ ተጋላጭ ከሆኑ ሰዎች ጋር የተያያዘ ምክረ ሃሳብ 58።

## የማስፈጸሚያ የጊዜ ሰሌዳ

ሁሉንም ምክረሃሳቦች በአራት ዓመት ውስጥ ተግብሮ ለማቅረብ በትክክለኛው መንገድ ላይ ነን። ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰው፡ ጥቂት ምክረሃሳቦች አዲስ ሕጋ ሳይወጣላቸው ሊተገበሩ ስለማይችሉ ይህ ያህል ግዜ ይወስድብናል ብለን እንጠብቃለን።

መስከረም ላይ ያስተዋወቅነው የየማስፈጸም የጊዜ ሰሌዳ ለእያንዳንዱ ምክረሃሳብ ቁልፍ ወሳኝ ደረጃዎችን እንዲሁም የሚጠበቁ ማጠናቀቂያ ግዜያችንን ያስቀምጣል። አዳዲስ ወሳኝ ደረጃዎችን ወይም በማስፈጸም የጊዜ ሰሌዳ ላይ ለውጥ ለማሳየት በእያንዳንዱ ሩብ ዓመት አዲስ መረጃዎችን እናቀርባለን (እናዘምናለን)።

ሁሉንም ምክረሃሳቦች በተገቢው ፍጥነት እና መዘግየቶችን በመቀነስ ለማስፈጸም መሰራታችንን እንዲሁም እነዚህ ስራዎች ለመቆጣጠር ጠንካራ አሰራሮችን ማስቀመጣችንን እንቀጥላለን። ለተለየ ምክረሃሳብ የተቀመጠ የጊዜ ሰሌዳ መስተካከል ካለበት በአፈጻጸም የግዜ ሰሌዳ ላይ በግልጽ እንዘረዝራለን እንዲሁም የዘገየበትን ምክንያት እና የሚፈጥረውን ተጽእኖ በተመለከተ በግልጽ እናሳውቃለን።

## የየካቲት ዓመታዊ ሪፖርት

በየካቲት 2025 ምላሽ ለግሬንፈል ታወር ማጣሪያ ደረጃ 2 ሪፖርት፡ ለፓርላማ በየአመቱ ሪፖርት ማድረግ ላይ በርትተን እሰራለን። ይህ ለግልጽነት በቀጣይ የምናደርገው ጥረት ክፍል ነው እንዲሁም ሂደቶቻችን ለቁጥጥር እና ክትትል ክፍት ማድረጋችንን እናረጋግጣለን።

የመጀመሪያ ዓመታዊ ሪፖርት የካቲት 2026 ላይ ይታተማል። ይህም የቃል እና የጽሑፍ መግለጫዎችን ለፓርላማ ማቅረብን እንዲያጠቃልል እንጠብቃለን፤ሁለቱም እዚህ GOV.UK ገጽ ላይ እንዲገኙ ይደረጋል።

ለማድረግ ያዘጋጀነውን እንዲሁም እስከአሁን ያካሄድነውን ፣ የወደፊት ዓመት ዕቅዶችን እና ዘላቂ ለውጦችን የማምጣት ሃላፊነታችንን በተመለከተ አጠቃላይ ሰፊ እይታ በማቅረብ ለማጣሪያው በምንሰጣቸው ምላሾች ላይ እንገነባለን።

ዓመታዊውን ሪፖርት ተከትሎ፡2027 ላይ ወደ ፓርላማ ሪፖርት ደግመን ከማቅረባችን በፊት ግንቦት፣ መስከረም እና ታሕሳስ ወር ላይ የሩብ ዓመት ሪፖርታችንን እንቀጥላለን።

## ሰፋ ያለ ማሻሻያዎችን በተመለከተ አዲስ መረጃ

### የአደጋ ስጋቶችን ማስወገድ ስራን የማፋጠን እቅድ (RAP)

ከየካቲት 2025 ጀምሮ፡ ክፍሉ 5,570 የመኖሪያ ቤቶች ህንጻዎችን እና የ11 ሜትር እና በላይ ርዝማኔ ያላቸውን ፈትሿል እናም ደህንነቱ ያልተጠበቀ የውጪ ሽፋን እንዳላቸው አረጋግጧል። የዩናይትድ ኪንግደም የመኖሪያ ቤቶች፣ ማሕበረሰቦች እና አካባቢ መስተዳድሮች ሚኒስቴር (MHCLG) የሚያካሄደው የአደጋ ስጋት ማስወገድ ስራ አካል ሆኖ 11 ሜትር እና በላይ ርዝማኔ ላላቸው ሁሉም ህንጻዎች በግምት 65-97% ለሚሆኑት የአደጋ ስጋት ማስወገድ ስራ እንዲሰራላቸው ይጠበቃል።

ደህንነቱ ያልተጠበቀ የውጪ ሽፋን እንዳላቸው ከታወቁ 5,570 ህንጻዎች 2,705 (49%) የአደጋ ስጋት ማስወገድ ስራ ተጀምሮላቸዋል ወይ ተፈጽሞላቸዋል ከነዚህ ውስጥ 1,946 (35%) የአደጋ ስጋት ማስወገድ ስራ ተፈጽሞላቸዋል። ይህም የሰማይ ጠቀስ (18 ሜ በላይ) እና ግማሽ ሰማይ ጠቀስ (11-18 ሜ) ርዝማኔ ላላቸው ህንጻዎች የሚካሄድ የአደጋ ስጋት ማስወገድ ስራ ያጠቃልላል።

የመጨረሻው ወርሃዊ [የህንጻ አደጋ ስጋት ማስወገድ ስራ መረጃ] ሕዳር 20 2025 ላይ ታትሟል።

# የከፍተኛ ስጋት ህንጻዎች ቁጥጥር አሰራር

የከፍተኛ ስጋት ህንጻዎች (HRB) ቁጥጥር አሰራር ከተዋወቀበት እንዲሁም የህንጻዎች ደህንነት ቁጥጥር (BSR) (BSR) ከተመሰረተበት ቀን ጀምሮ ወደ ደህንነት ያላልቸውን ህንጻዎች ወደ መገንበት እና መመሪያን ወደ መከተል የተሻለ ባህል መንቀሳቀስ ጀምረናል።

ይሁን እንጂ፡ የባለስልጣኑ አሰራሮች አንዳንድ ያልተጠበቁ ውጤቶችን እንዳስከተለ እንረዳለን፤ ማለት አመልካቾች ከፍተኛ የአደጋ ስጋት ላላቸው ህንጻዎች ለተለመደ ግን አስፈላጊ የግንባታ ዓይነት ስራዎችን ለመስራት ፈጣን የህንጻዎች ደህንነት ቁጥጥር (BSR) (BSR) ማረጋገጫ ማግኘት ላይ።

በተለይ፡ ከፍተኛ የአደጋ ስጋት ያላቸው ህንጻዎች ቁጥጥር ሂደትየሚጠይቃቸው ጥቂት የሁለገብ አሰራሮች ያለተመጣጠነ የጊዜ እና የዋጋ መመዘኛዎችን ሊያቀርቡ እንደሚችሉ በዚህም ከፍተኛ አደጋ ስጋት ባላቸው ህንጻዎች ላይ አንዳንድ የስራ ዓይነቶችን በፍጥነት የማከናወን ችሎታዎችን እንደሚገድቡ ተረድተናል። በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ይህ አስፈላጊ ስራዎችን እና ሌሎች ለደህንነት በጣም ወሳኝ የሆኑ ስራዎችን እንዳይከናወኑ ወደ ማዘግየት ሊያመራ ይችላል በዚህ የተነሳም ከፍተኛ ስጋት ባለባቸው ህንጻዎች ውስጥ በሚኖሩ ነዋሪዎች እና የህንጻ ተጠቃሚዎች ላይ ያልተሟላ ደህንነት እና ጤና ስጋት ሊፈጥሩ ይችላሉ።

አስፈላጊ የህንጻ ደህንነት እና ብቃት ደረጃዎችን በመጠበቅ የቁጥጥር አሰራሩ ተገቢ መሆኑን ለማረጋገጥ በአስቸኳይ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል።

ለዚህም ነው፡አሁን በከፍተኛ ስጋት ቁጥጥር አሰራር ስር በሚገኙ ህንጻዎች ላይ በመካሄድ ላይ የሚገኙ አንዳንድ የስራ ዓይነቶችን የመቆጣጠር ሂደት ተመጣጣኝነትን ለማሻሻል፡ አዲስ ዓመት ላይ ባቀረብናቸው ሃሳቦች ላይ አስተያየቶችን ለመሰብሰብ የምንመካከረው (ከነዋሪዎች እና ኢንዱስትሪው ጨምሮ)።

ምክክሩ፡ ከፍተኛ የአደጋ ስጋት ወዳለባቸው ህንጻዎች የሚቀጥሉ የፋይበር ኦፕቲክስ ገመድ መዘርጋትን በተመለከተ ሃሳቦችን ከማቅረብ ጋር፡ በስፋት በሚሰራባቸው እና በሚከተሉት በከፍተኛ የአደጋ ስጋት ባላቸው ህንጻዎች ላይ በሚሰሩ የግንባታ ስራ ዓይነቶች የቁጥጥር አሰራር መመዘኛዎች አስተያየቶችን ይጠይቃል፡ ፋይበር ኦፕቲክስ ኬብል መዘርጊያ በውስጥ ግድግዳዎች ቀዳዳዎችን መብሳት፣ የሞባይል ግንኙነት ማማ ስራ፣ እንዲሁም አሁን ባለው የእሳት መከላከያ በሮች ላይ የሚሰራ ስራ። የፋይበር ኦፕቲክስ ኬብል መዘርጋትን በተመለከተ፡ ከከፍተኛ የአደጋ ስጋት ካለባቸው ህንጻዎች ውጪ ባሉ ህንጻዎች ላይ የሚደረገውንም የህንጻ ቁጥጥር ሂደት ጨምሮ። በተጨማሪም፡ለወደፊቱ ለእነዚህ ስራዎች፡ የራስ ብቃት ማረጋገጫ ዕቅዶችን የማስቀመጥ አዋጭነት በተመለከተ አስተያየቶችን እንጠይቃለን።

በተጨማሪም፡ በእነዚህ ሃሳቦች ላይ ከህንጻዎች ደህንነት ቁጥጥር (BSR) ጋር መደበኛ ምክክር እናደርጋለን። በስፋት በሚሰራባቸው የቁጥጥር አሰራር መመዘኛዎችን በተመለከተ ውይይት እያካሄድን የግንባታ ስራ በማካሄድ ላይ የሚገኙት የግንባታ ህግ ደረጃዎችን እንዲያሟሉ ይጠበቅባቸዋል።

## ማህበራዊ መኖሪያ ቤት ማሻሻያዎች

መሰከረም 30 ላይ የማህበራዊ መኖሪያ ቤቶች ተቆጣጣሪ የመኖሪያ አባላት ብቃት እና ስነስርዓትን እና መረጃ ማካፈልንበተመለከተ አዲስ ህጎችን እንዲያወጣ ትእዛዝ ሰጠን። አዳዲስ የብቃት ደረጃዎች ከጥቅምት 2026 ጀምሮ ስራ ላይ ይውላሉ። እንዲሁም የመረጃ ነጻነት መብቶች ለተከራይ አስተዳደር ድርጅት አባላት ተከራዮች እንዲሰጥም እንጠይቃለን።

ደረጃ አንድ የአዋብ ህግ ጥቅምት 27 ላይ ጀምሯል። ይህ ማለት የቤት አከራዮች ከባድ እርጥበቶችን፣ ሻጋታዎችን እና ሌሎች አስቸኳይ ችግሮችን በተጠቀሰው የግዜ ሰሌዳ ሊያጸዱ ይገባል። ከ2026 እስከ 2027 ባለ ግዜ ውስጥ፡ከመጨናነቅ ውጪ፡ ሁሉንም በመኖሪያ ቤቶች ጤና እና ደህንነት ደረጃ አሰራር ስር የተዘረዘሩትን አደጋዎች ለማጠቃለል መንግስት ህጎችን ያሰፋል።

ህዳር 1 ላይ አዲስ ህጎች ወጥተዋል፡ ይህ ማለት አካራዮች በየ አምስት ዓመቱ አዲስ ተከራዮች ላይ እጅግ ጥብቅ የኤለክትሪክ ደህንነት ቁጥጥሮችን ማካሄድ አለባቸው። በተጨማሪም የሚያቀርቧቸውን ማናቸውንም የኤለክትሪክ መገለገያዎች መፈተሽ አለባቸው። እነዚ ህጎች ከግንቦት 2026 ጀምሮ በሁሉም ተከራዮች ላይ ተግባራዊ ይሆናሉ።

የጥሩ ቤቶች ደረጃ እና ዝቅተኛ የጉልበት ውጤታማነት ደረጃዎችን በተመለከተ የህዝብ ምክክሮች መስከረም ላይ ተዘግቷል። ቀጣይ እርምጃዎችንን ከመዘርዘራችን በፊት መልሶችን ግምት ውስጥ እናስገባለን።

የ ማህበራዊ መኖሪያ ቤቶች ፈጠራ ፈንድ ጥቅምት 27 ላይ ተጀመረ። ይህ ፈንድ፡ ተከራዮችን፣ የማህበራዊ መኖሪያ ቤቶች አከራዮች እና ሌሎች ድርጅቶች ተከራዮች መኖሪያ ቤታቸውን እና የአከራዮች አገልግሎቶችን የሚነኩ ውሳኔዎችን በተመለከተ የበለጠ የድምጽ ማሰማት ዕድል የሚሰጡ አዳዲስ ሃሳቦችን እንዲያመነጬ ያግዛል።

የማመልከቻ ሂደትን ተከትሎ ከ130 በላይ አዲስ አባላት የዕድገት ፖሊሲዎችን ቅርጽ ለማስያዝ፡ አስተያየቶቻቸውን እና ልምዳቸውን ለማካፈል የማህበራዊ መኖሪያ ቤቶች ነዋሪዎች ፓነል ተቀላቅለዋል።

ሚኒስተሮችበተከራይ የሚመራ የብሄራዊ ተከራዮች ድምጽ የመመስረት ሃሳባቸው ላይ ለመወያየት እና አንዳንድ ተከራዮች የሚያጋጥማቸውን መገለልን ለመፍታት ከብዙ የተከራይ ቡድኖች ጋር ተገናኝተዋል።

## ግልጽነት እና ቁጥጥር

ምክረሃሳብ 25 በመርህ ደረጃ ተቀብለነዋል እንዲሁም ከግሬንፈል ታወር ማጣሪያ ደረጃ 2 ሪፖርት እና የግንቦት 2024 የተበከለ ደም ማጣሪያ ሪፖርት የተገኙ የምክረሃሳቦችን ተፈጻሚነት የሚከታተል ሃምሌ ወር ላይ የመጀመሪያውን የህዝብ ማጣሪያዎች፡ምክረሃሳቦች እና የመንግስት ምላሾችን ዳሽቦርዶችን አስጀምረናል። ዳሽቦርዶቹ የመንግስት ትግባሬዎች አዳዲስ መረጃዎችን በማካተት እና በየሩብ ዓመቱ በማደስ ከ2024 ጀምሮ የሚኖሩ ሁሉንም ማጣሪያዎች ወደ ማካተቱ ያድጋል።

ሕዳር 14 ላይ የታተመውየመጨረሻው አዲስ መረጃ ፡በማንቸስተር አሬና ማጣራቶች፣ የግሬንፈል ታወር ማጣራቶች፣ የኰቪድ-19 ማጣራቶች ሞጁል 1 እና የተበከለ ደም ማጣሪያ ምክረሃሳቦች የዕድገት አዲስ መረጃዎችን ያጠቃልላል። ይህ

ለግልጽነት ያለው ቁርጠኝነት በምክረሃሳቦቹ መሰረት፡ የህዝብ ቁጥጥርን እና ተጠቃሚነትን ያጠናክራል። አሁን ይህ ምክረሃሳብ ተዘግቷል እንዲሁም ሙሉ በሙሉ ተተግብሯል።

## ምክረ-ሃሳቦች ላይ ማጠቃለያ ዝማኔ

ይህ ክፍል ካለፈው የመስከረም 2025 የሂደት ሪፖርት ምክረ ሃሳቦችን ለመተግበር ሲሰሩ የቈዩ ስራዎች ማጠቃለያ ዝማኔ ያቀርባል። አጣሪው በሚጠቀምባቸው ጭብጦች ተበዳድኗል።

የሚከተሉትን ማስፈንጠሪያዎች በመጠቀም በሁሉም ምክረ-ሃሳቦች ላይ ዝርዝር ዝመናዎችን ማግኘት ይችላሉ፡

- የግንባታ ኢንዱስትሪው
- የእሳት እና የነብስ አድን አገልግሎቶች
- ምላሽ እና ማገገም
- ለአደጋ ተጋላጭ ሰዎች

## የግንባታ ኢንዱስትሪ

## ነጠላ የግንባታ ተቆጣጣሪ

የህንጻዎች ደህንነት ቁጥጥር (BSR)ን በማጠናከር አሁን ያሉትን የቁጥጥር አሰራሮች በሚደግፉ ስራዎች በመጀመር፡ በመስከረሙ የሂደት ሪፖርት ውስጥ የነጠላ ግንባታ ተቆጣጣሪን የመተግበር ሂደትን በተመለከተ አዲስ መረጃ አቅርበናል። ህዳር ላይ፡ ከጤና እና ደህንነት ስራ አስፈጻሚ የግንባታ ደህንነት ተግባሮችን ወደ አዲሱ ገለልተኛ አካል የሚያስተላልፉ በህግ የተቀመጡ መገልገያዎችን አስቀምጠናል።

የህንጻዎች ደህንነት ቁጥጥር (BSR) ላይ የሚደረጉ ለውጦች ላይ በመጨመር፡ ዛሬ (17 ታሕሳስ 2025) ላይ ነጠላ የግንባታ ተቆጣጣሪ ዝርዝር መረጃ እና ምክክር ታትሟል። ዝርዝር መረጃው ፡ የመንግስት ለማጣሪያውን ምክረሃሳብ ያለው ቁርጠኝነትያረጋግጣል እንዲሁም የነጠላ የግንባታ ተቆጣጣሪ የማቀርብበትን መንገድ በተመለከተ በዝርዝር ያቀርባል። ዝርዝር መረጃው በተጨማሪ፡የቁጥጥር ለውጦችን በተራዘመ፣ በአሰራር ደረጃ አቀራረብ አማካኝነት ከማጣሪያ ምክረሃሳቦች አልፎ የመሄድ ጠንካራ ፍላጎታችንን ያስቀምጣል እንዲሁም የፍላጎታችንን ቁልፍ ትኩረቶች ያስረዳል።

## ከፍተኛ ስጋት ያለባቸው ህንጻዎች ትርጉም

ከፍተኛ ስጋት ያለባቸው ህንጻዎች ትርጉም እንዲገመገም የሚጠይቅ ምክረሃሳብ ተሟልቷል አንዲሁም ሙሉ በሙሉ ተለቋል። ዛሬ (17 ታህሳስ 2025)፡ የህንጻዎች ደህንነት ቁጥጥር (BSR) የመጀመሪያ ግምገማቸውን በመቀጠል ላይ ካለው የግምገማ ዕቅድ ጎን ለጎን አትመዋል። የመጀምሪያው ግምገማ ፡ የአሁኑ ትርጉም የእሳት መስፋፋት እና የመዋቅር ብልሽቶች ግለሰቦች ላይ የፈጠረውን ስጋት የሚያሳይ ማስረጃ በተገቢ ሁኔታ እንደሚያንጸባርቅ አሳይቷል። ስለዚ ፡ የህንጻዎች ደህንነት ቁጥጥር (BSR) ምክረሃሳብ፡በአሁኑ ጊዜ መጠነስፋቱን እንዳይለወጥ ነው። ይህ የመኖሪያ ቤቶች፣ ማሕበረሰቦች እና አካባቢ መስተዳድሮች ሚኒስቴር (MHCLG) በጥንቃቄ የተመረምረ እና ተቀባይነት ያገኘ ነው።

የህንጻዎች ደህንነት ቁጥጥር (BSR) በከፍተኛ ስጋት ያለባቸው ህንጻዎች ትርጉም ላይ ቀጣይነት ያለው ግምገማ ያካሂዳል። ይህም፡የከፍተኛ ስጋት ህንጻዎች ቁጥጥር አሰራር የተጠናከረ የቁጥጥር ቅኝት ስር ያሉ ህንጻዎች ዝርዝር በማንኛውም መንገድ መሻሻል አለባቸው ወይ የሚለውን ለመወሰን ግለሰቦች ላይ የሚፈጠሩ ስጋቶች መረጃ እና ማስረጃ በየጊዜው መፈተሻቸውን ያረጋግጣል።

## የመንግስት አሰራሮች

ቢዝነስ እና ንግድ ክፍል ውስጥ የሚገኘው ብሔራዊ የግንባታ ውጤቶች ቁጥጥር በሴክረተሪ ኦፍ ስቴ ስር ላለው የመኖሪያ ቤቶች፣ ማሕበረሰቦች እና አካባቢ መስተዳድሮች ሚኒስቴር (MHCLG) ሪፖርት ያደርጋል እናም በሪፖርቱ የድርጅቶች ለውጥ ሰፊ ምክረ-ሃሳብ መሰረት የሚዋሃዱበትን መንገድ መፈለጋችንን እንቀጥላለን።

ከሚያዚያ 1 2025 ጀምሮ ሁሉም ከእሳት አደጋ ጋር የተያያዙ ተግባሮች ጋር የተያያዙ የሚኒስትር ሃላፊነቶች ከሆም ኦፊስ ወደ የመኖሪያ ቤቶች፣ ማሕበረሰቦች እና አካባቢ መስተዳድሮች ሚኒስቴር (MHCLG) ተላልፈዋል። እንዲሁም ሃምሌ 2025 ሁሉም የሚመለከታቸው የሆም ኦፊስ አባላት ወደ የመኖሪያ ቤቶች፣ ማሕበረሰቦች እና አካባቢ መስተዳድሮች ሚኒስቴር (MHCLG) ሽግግር ተካሄዷል። የበጀት ሽግግሩ ጸድቋል ግን ይህ ምክረሃሳብ ፡ የፓርላማ የድጋፍ ግምትቶች ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ ሊተገበር አይችልም። መንግስት፡ የእሳት አደጋ ስራዎች በሙሉ ወደ የመኖሪያ ቤቶች፣ ማሕበረሰቦች እና አካባቢ መስተዳድሮች ሚኒስቴር (MHCLG) በማስተላለፍ (ለእሳት አደጋ ደህንነት ሃላፊነት ብቻ ሳይሆን) ከማጣሪያ ምክረሃሳብ በላይ አልፎ ሄዷል።

## የእሳት አደጋ መሐንዲሶች

የእሳት አደጋ መሃንዲስነት ሙያን በተመለከተ ለመንግስት የልዩ ባለሙያ እና ትምህርታዊ ምክሮችን ለማቅረብ የስጋ አደጋ መሃንዲሶች አማካሪ ፓነል ሚያዚያ ላይ ተመሰረተ። በምክረሃሳብ 17 መሰረት፡ ብቃቱ ከተረጋገጠ የእሳት አደጋ መሃንዲስ በሚጠበቁ ክህሎቶች እና እውቀቶች ተፈጻሚነትን የሚያስገድድ ስልጣን እና አስፍላጊነት ያለው መግለጫ ተዘጋጅቶ ነበር። በዘርፉ ተሳትፎ መረጃ የታገዘ ይህ ስራ፡የበለጠ ወጥነት ያለው እና ተጠያቂ ሙያን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቁልፍ እርምጃ ነው። ተፈጻሚነትን የሚያስገድድ ስልጣን እና አስፍላጊነት ያለው መግለጫ፡ስነምግባርን በመደገፍ እና የህዝብ ተአማኒነትን ደግሞ ለመገንባት በማገዝ፡ የስራ ድርሻዎችን፣ ሃላፊነቶችን እና የሚጠበቁ የሙያ ብቃት ደረጃዎች ይተረጉማል። የወደፊት ህግን ሊያረጋግጡ የሚገቡ ብዙ ቁልፍ መርሆዎችን ይዘረዝራል እንዲሁም ከ 15 እስከ 18 ያሉ ምክረሃሳቦችን ለመተግበር የተቀናጀ አቀራረብ አካል ነው።

ዛሬ (ታህሳስ 17 2025) ክፍሉ ተፈጻሚነትን የሚያስገድድ ስልጣን እና አስፍላጊነት ያለው መግለጫ ከ ቀጣይ እርምጃ ወረቀት ጎን ለጎን አትሟል። ይህ ወረቀት ፡ብቅ እያሉ ያሉትን የሙያ ህጎችን ጨምሮ፡ ተፈጻሚነትን የሚያስገድድ ስልጣን እና አስፍላጊነት ያለው መግለጫ፡ከሰፊው ማሻሻያ ጋር ምን ያህ እንደሚገጥም ለዘርፉ ግልጽ በማድረግ፡ ምክረሃሳቦች 15,16 እና 18 በተመለከተ የክፍሉን የታቀደ አቀራረብ ይዘረዝራል።

### የግንባታ ቁጥጥር

የግንባታ ቁጥጥር ገለልተኛ ፓነል፡ በየጊዜው መገናኘት እና ምክረሃሳቦቹን ለመንግስት በንቃት ማቅረቡን ቀጥሏል። መንግስት በአዲሱ ዓመት መደበኛ ምላሽ ለማውጣት ካቀደው ጋር፡ የመጨረሻውን ሪፖርት በሚቀጥሉት ወራት ለማተም ዝምምነት ተደርሷል።

## የእሳት እና ነብስ አድን አገልግሎቶች

### የእሳት እና ነብስ አድን ኰሌጅ

አዲሱ የእሳት እና ነብስ አድን ኰሌጅ ማተኰር በሚገባው ስኬት፣ ማሳካት ስለሚገባው ተግባሮች እና ማቅረብ ስለሚችልባቸው መንገዶች በተመለከተ አስተያየቶችን ለመሰብሰብ የህዝብ ምክክሮችን ማካሄድ ላይ ተግተን እንሰራለን። የመኖሪያ ቤቶች፣ ማሕበረሰቦች እና አካባቢ መስተዳድሮች ሚኒስቴር (MHCLG) በምክክር ላይ ሊካተቱ የሚችሉ ሃሳቦችን ለማጎልበት እሳት አደጋ ዘርፍ ላይ ካሉ ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የስራ እና መጨረስ ቡድን መስርቷል። ምክክር፡ የግሬንፈል ታወር ማጣራት ሪፖርት የሚጠብቃቸውን ነገሮች የበለጠ እንዲያሟላ ለማድረግ እንዲሁም የተጠናከረ የማስረጃ መሰረት ለመስብሰብ እንዲያስችለን በሚቀጥለው ዓመት ምክክር ለማካሄድ አቅደናል።

### የብሄራዊ እሳት አደጋ ዋና አለቆች ምክርቤት(NFCC) እና የለንደን እሳት አደጋ ብርጌድ (LFB)

የብሄራዊ እሳት አደጋ ዋና አለቆች ምክርቤት(NFCC) ስራ ስምምነት በተደረገባቸው የአቅርቦት እና እርምጃ ውጥን መሰረት መሻሻሉን ቀጥሏል። የተለያዩ ብሄራዊ መመሪያ ክፍሎች እና የመማሪያ መገልገያዎች በተገቢ የአምራር መንገዶች ወደ ህትመት እንዲሸጋገሩ፡ ግምገማ ተካሄዶባቸዋል እንዲሁም የለውጥ ሃሳቦች እና ጭማሪዎች ተደርጎባቸዋል። የመጀመሪያው የተሻሻለ መመሪያ፣በቦታ የተለየ የአደጋ መረጃ፣ እና ሊፍቶች እና የሊፍት ቁልፎች ጥቅምት 23 2025 ላይ ታትሟል።

የሊፍ ቁልፎች ተገቢ መመሪያዎችን እና የብቃት ደረጃዎችን ለማረጋገጥ እና በሁሉም የሊፍት ኢንዱስትሪ የበለጠ የጥራት ደረጃ ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን በተመለከተ የየብሄራዊ እሳት አደጋ ዋና አለቆች ምክርቤት(NFCC) አቋም ስምምነት ተደርሶበታል እንዲሁም ለየህንጻዎች ደህንነት ቁጥጥር (BSR) ተነግሯል። የብሄራዊ እሳት አደጋ ዋና አለቆች ምክርቤት(NFCC) የፈጣን ምላሽ ቅኝት አሰራር (FRSs) የውሃ አቅርቦትን በተመለከተ እያጋጠመው ያለውን ችግሮች የሚያጎላበት እና አወንታዊ ለውጦችን እንዲመጡ የሚያደርግባቸው ዕድሎችን በመስጠት ከውሃ አገልግሎት ቁጥጥ ባለስልጣን (Ofwat ) ጋር የስራ ግንኙነት ቀጥሏል።

## ምላሽ እና ማገገም

የመኖሪያ ቤቶች፣ ማሕበረሰቦች እና አካባቢ መስተዳድሮች ሚኒስቴር (MHCLG) የአካባቢያዊ መቋቋም ብቃት ላይ ጠንካራ ዕድገቶች አሳይቷል። አሁን ዕቅዶቻቸውን በመተግበር ላይ ለሚገኙ ለሁሉም አምስት የአካባቢያዊ መቋቋም ብቃት ፎረሞች ተከላካዮች ፈንድ (ገንዘባዊ ድጋፍ) ቀርቧል እንዲሁም የመጀመሪያው ዋና የመቋቋም ብቃት ኦፊሰር

ተመርጧል። ብሄራዊ ቡድን የእኩያ ግምገማ ፕሮቶኮልን ዲዛይን ለማውጣት በየጊዜው ተገናኝተዋል በዚህም ዋና ይዘቶቹ ላይ ተስማምተዋል እንዲሁም ጸደይ ወራት ላይ በደንብ ሊሻሻል እና ሊሞከር የሚችል ረቂቅ አዘጋጅተዋል። የመኖሪያ ቤቶች፣ ማሕበረሰቦች እና አካባቢ መስተዳድሮች ሚኒስቴር (MHCLG) ካካቢኔ ጽሕፈት ቤት(CO) ጋር በጋራ ለአካባቢ መስተዳድሮች ስልተና ለመስጠት እና በተካሄዱ የመቋቋም ብቃት ስልጠናዎች ሪፖርቶችን ማዘጋጀት ላይ ለማገዝ፡ ከአካባቢ መስተዳድር ማህበር(LGA) ፣ የአካባቢ መስተዳድር የበላይ ስራ አስኪያጆች ማህበር (SOLACE) እንዲሁም የዩኬ የመቋቋም ብቃት አካዳሚ(UKRA) ጋር ጠንካራ የስትራቴጂ ጥምረት መመስረታቸውን ይቀጥላሉ። የመኖሪያ ቤቶች፣ ማሕበረሰቦች እና አካባቢ መስተዳድሮች ሚኒስቴር (MHCLG) የዩኬ መንግስት መቋቋም እርምጃ ዕቅድን በመላው የአካባቢ መዋቅሮች ውስጥ ለማስገባት እንዲሁም በብሄራዊ እና አካባቢያዎ መንግስ መካከል ትብብሮችን የማጠናከር ጥረቶችን መደገፉን ይቀጥላል።

## ለአደጋ ተጋላጭ ሰዎች

### የመኖሪያ ቤቶች ግላዊ የአደጋ ጊዜ ሽሽት ዕቅዶች (RPEEPs)

የመኖሪያ ቤቶች ግላዊ የአደጋ ጊዜ ሽሽት ዕቅዶች (RPEEPs) ሃምሌ 4 2025 ላይ የተመሰረቱት የእሳት ደህንነት (የመኖሪያ ቤቶች ሽሽት ዕቅዶች (ኢንግላንድ) ህጎች፡ከሚያዚያ 6 2026 ጀምሮ ይታዘዛሉ። እነዚህን ህጎች ተፈጻሚነት ላይ የሚመለከታቸው ሰዎች መመሪያ ታሕሳስ 2 2025 ላይ ታትሟል።